# ከንግድ አሰራር ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ለውጦችን ስለማሳወቅ የወጣ መመሪያ ቁጥር 143/2011

መጋቢት/2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ከንግድ አሰራር ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ለውጦችን ስለማሳወቅ የወጣ መመሪያ ቁጥር 143/2011

ግብር ከፋዩ ከሚያከናውነው የንግድ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በየጊዜው የሚያደርጋቸውን ለውጦች ለግብር ባለስልጣኑ ስለሚያሳውቅበት ሁኔታ በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የገቢዎች ሚኒስቴር በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 10(1) (መ) በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ከንግድ አሰራር ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ለውጦችን ስለማሳወቅ የወጣ መመሪያ ቁጥር 143/2011 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፣

1/ **"ለውጥ"** ማለት በታክስ ከፋዩ የሚደረጉ የስም፣ የቋሚ አድራሻ፣ የፖስታ አድራሻ፣ የመተዳደሪያ ደንብ ፣ የባንክ ሂሳብ አድራሻ ፣ የንግድ ስራ እንቅስቃሴ እና ሌሎችም ተመሳሳይ ለውጦች ማለት ነው፡፡

2/ **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት"** ማለት በግለሰብ ታክስ ከፋይ ላይ የደረሰ ከባድ ወይም ጽኑ ህመም ወይም ሞት ሲሆን ለድርጅት ደግሞ በታወቀ የፀጥታ ችግር ምክንያት እንቅስቃሴን የሚገታ ሁኔታ ማለት ነው፡

3/ "**ከባድ ወይም ጽኑ ህመም**" ማለት የንግድ ስራ እንቅስቃሴውን የሚመራለት የታክስ እንደራሴ የሌለው ግለሰብ ታክስ ከፋዩ በለውጥ ማስታወቂያ ጊዜ ውስጥ ተንቀሳቅሶ ለውጡን ማስታወቅ የማይችልበት እና እውቅና ባለው የህክምና ተቋም እየተረዳ ያለበት ሆኖ በማስረጃ የሚረጋገጥ ህመም ነው፡፡

4/ "**ሚኒስቴር**" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ገቢዎች ባለስልጣን ማለት ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቶቻቸውንም ይጨምራል፡፡

5/ በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማንኛውም ታክስ ከፋይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ታክስ ከፋዩ የሚያሳውቃቸው ለውጦች

1/ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ከዚህ በታች የተመለከተው ለውጥ ሲያደርግ ለውጡ በተደረገ በ30 ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

ሀ) በንግድ ድርጅቱ ስያሜ ላይ የተደረገ ለውጥ፣

ለ) በድርጅቱ ስም የተመዘገበ

(1) ቋሚ የንግድ ሥራ፣ የቢሮ እና የመኖሪያ አድራሻ ለውጥ፣

(2) በማምረቻ ቦታ ወይም ታክስ ከፋዩ በሚጠቀምበት መጋዘን ላይ የተደረገ የአድራሻ ለውጥ፣

(3) በፖስታ ወይም በመደበኛ እና በተንቀሳቃሽ ስልክ፤ ፋክስ ወይም ኢ-ሜይል አድራሻ ላይ የተደረገ ለውጥ፣

ሐ) በዋንኛ የሥራ እንቅስቃሴው ወይም በቅርንጫፍ ወይም በንግድ ሥራው ዘርፍ ወይም መስክ ላይ የተደረገ ለውጥ ፣

መ) በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ወይም የመመስረቻ ጽሁፍ ወይም የሽርክና ስምምነት ላይ የተደረገ ለውጥ፣

ሠ) በአክስዮን ባለድርሻ አባላት ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ረ) በድርጅቱ ወይም በታክስ እንደራሴው የባንክ ሒሳብ ወይም የባንክ ቅርንጫፍ አድራሻ ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ሰ) በታክስ እንደራሴው እና ከሚኒስቴሩ ጋር ግንኙነት በሚያደርግበት የኤሌክትሮኒክስ አድራሻ ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ሸ) በተመዘገበና በተከፈለ ካፒታል ላይ የተደረገ ለውጥ፤

ቀ) የንግድ ሥራውን በከፊል ወይም በሙሉ በማቋረጥ ወይም በሽያጭ ወይም በስጦታ በማስተላለፍ ወይም በመለወጥ ወይም በዋስትና በማስያዝ በድርጅቱ ላይ የተደረጉ ለውጦች፣

በ) በንግድ ሥራ ወኪል ወይም የታክስ እንደራሴ ላይ የተደረገ ለውጥ፣

ተ) የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ለካፒታል ማሳደጊያ ሲውል፣

ቸ) የገቢ ምንጭ መቋረጥን ወይም መሻሻልን በተመለከተ፣

(1) የቤት ወይም የህንፃ ወይም የመጋዘን ኪራይ ውል ሲቋረጥ ወይም ሲሻሻል ፤

(2) በተሽከርካሪ ወይም በኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ወይም ሌሎች የካፒታል ወይም የንግድ ስራ ዕቃዎች የተደረገ የኪራይ ውል መቋረጥ ወይም መሻሻል፣

(3) በራሱ ገቢውን የሚስታውቅ ተቀጣሪ ስራውን ሲለቅ ወይም ሲቀይር ወይም የደመወዝ ለውጥ ሲኖር፣

(4) የንግድ ስራ እንቅስቃሴውን በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ሲያቋርጥ ወይም ሲያሻሽል ፣

ኃ) ታክስ ከፋዩ ሠራተኛ ሲጨምር ወይም ሲቀንስ ወይም የሠራተኞች የደመወዝ ለውጥ ሲያደርግ፤

2/ ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት ለውጦች የተለየ ለውጥ ማሳወቅ ያለበት ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ የለውጡን አይነት በሰርኩላር ያሳውቃል፡፡

## 5. የለውጥ ማስታወቂያ ቅጽ

ሚኒስቴሩ፣

1/ ታክስ ከፋዩ ለውጥ የሚያሳውቅበትን ቅጽ ያዘጋጃል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተዘጋጀው ቅጽ እንዳስፈላጊነቱ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለታክስ ከፋዮች ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት በሚዘረጋው የኤሌክትሮኒክስ ማሳወቂያ ዘዴ ታክስ ከፋዩ የሚልካቸውን የለውጥ ማሳወቂያዎች ይቀበላል፡፡

## 6. ለውጥን ስለማሳወቅ

1/ ታክስ ከፋዩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 መሰረት የተዘጋጀውን የለውጥ ማሳወቂያ ቅጽ በማንዋል ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመሙላት ታክስ ለሚከፍልበት ቅ/ጽ/ቤት ለውጡ በተደረገ በ 30 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1)መሰረት የሚቀርብ የለወጥ ማስታወቂያ የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማረጋገጫ ከተሞላው ቅጽ ጋር በማያያዝ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3/ በዚህ መመሪያ መሰረት የለውጥ ማስታወቂያ ቅጽ ተሞልቶ የሚቀርበው በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ እንደራሴ ወይም በታክስ ወኪሉ ብቻ ይሆናል፡፡

## 7. ለውጥን አለማሳወቅ ወይም ዘግይቶ ማሳወቅ

1/ በዚህ መመሪያ መሰረት ለውጡን በ30 ቀናት ውስጥ ያላስታወቀ ታክስ ከፋይ በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ቢኖርም የ 30 ቀን ጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ የለውጥ ማስታወቂያ የሚያቀርብ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀናት ብር 300 ይቀጣል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ቢኖርም ለውጥን ዘግይቶ በማስታወቅ የሚጣለው መቀጫ ከብር 20,000(ሀያ ሺህ ብር) ሊበልጥ አይችልም፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ላይ የተገለጸው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ለውጡን ያላስታወቀው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ እና ማስረጃው ተቀባይነት ካገኘ ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት እንደተወገደ የለውጥ ማስታወቂያውን ማቅረብ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከተው መቀጫ ተፈጻሚ አይሆንበትም፡፡

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

8. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስትር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**2011 ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**
**የገቢዎች ሚኒስቴር**
**ሚኒስትር**